# በድርድሩ የህዝቡ ፍላጎት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል

ስሜነህ

ካለፉት 25 አመታት ወዲህ በተለይ ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስታችን ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት 1987 ዓ.ም ጀምሮ በህዝቦች የዘመናት ተጋድሎ እውን የሆነው የፌደራል ስርአት የህዝቦችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ዋና ማእቀፍ ያደረገ ነው። የእልቂትና የብተና ምንጭ የነበረውን የብዝሃንነት ችግር ከመሰረቱ በመለወጥ ሃገራችን ቀጣይነት ባለው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደሎች እንድታስመዘግብ የሚያስችል ያልተማከለ የፌዴራል ስርአት በመገንባት ላይ ይገኛል።

ይህ ያልተማከለ የፌዴራል ስርአት በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ስርነቀል ለውጦችን ስለማስከተሉም በተለያዩ አግባቦች ማረጋገጥ ተችሏል። ከሁሉ በፊት የዘመናት የአገራችን ጭቁን ህዝብች ጥያቄዎች የነበሩት ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት፣ የመናገር፣ የመፃፍ፣ ሃሳብን በተለያዩ መንገዶች በነፃነት የመግለፅ እንዲሁም የመደራጀትና የመዘዋወር ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊ መደረጋቸውና የመሳሰሉት በአብነት ሊነሱ ይችላሉ። ህዝቦች በየአካባቢያቸው ራሳቸውን የማስተዳደር፣ በቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸው በጥብቅ እንዲከበር ከማድረጉም በላይ ህዝቦች በአካባቢዊና በጋራ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን እንዲኖራቸው ማድረጉም በተመሳሳይ፡፡

ህዝቦች አካባቢያቸውን የማልማት እኩል መብት እንዲኖራቸው በመደረጉም በልማት ተሳታፊና በተሳተፉት ልክም ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ በልማት ወደኋላ የቀሩ አካባቢዎች እንኳን የማስፈፀም አቅማቸውን ለማጎልበትና የመሰረተ-ልማት አውታሮችን ለመዘርጋት የሚያስችል ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኙ በመደረጉ በየክልሉ የተመጣጠነ ልማት እንዲሰፍን ሆኗል፡፡ በዚህም አማካኝነት በህገመንግስቱ ላይ በጉልህ የሰፈረው  አንድ ጠንካራ ትስስር ያለው የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር ራዕይ በህዝቦች እኩልነት፣ መከባበርና መፈቃቀድ ላይ ተመስርቶ እንዲገነባ እያደረገና የማድረግም ሙሉ አቅም  እንዳለውም በተግባር እያረጋገጠ ነው።

በአገራችን እየተገነባ ያለው የፌዴራል ስርአት በትብብርና በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርአት ነው። ስርአቱ የዘመናት የብሄራዊና የመደብ ድርብ ጭቆና የህዝብ ጥያቄዎች ከመሰረቱ ለመለወጥ ከተከተላቸው ቁልፍ የፖለቲካ አቋሞችና ከወሰዳቸው ወሳኝ ፖለቲካዊ እርምጃዎች መካከል የአገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብቶችን ማረጋገጥ ቢሆንም ከዚሁ ባልተናነሰ አንድ የጋራ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር የመጨረሻው ግብ ሆኖ ተቀምጧል።

በዚህም አዲሲቷ ኢትዮጵያ በህዝቦች መፈቃቀድና እኩልነት ላይ የተመሰረተች፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚንፀባረቅባት አገር የመገንባት ራእይ ተቀርፆ እየተሰራ ይገኛል። ሰብእዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተሟላ ሁኔታ የሚከበሩባት፣ የዴሞክራሲ ባህልና ተቋሞች የሚያብቡባት፣ ህዝቡ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ህይወት የነቃ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎውን የሚያረጋግጥበት፣ በህዝቦች መብት መከበር፣ በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠንካራ አንድነት የሚጎለብትበት፣ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ የመድበለ ፓርቲ ስርአት መፍጠር የስርአቱ ዋነኛ አላማና ተልእኮ እንደሆነም በተለያዩ መንግስታዊ ሰነዶች ተመልክቷል።

ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣን እንደተጎናፀፉ ሁሉ በጋራ የተመሰረተው የፌዴራል ስርአቱንም የሚመሩት ከየክልሉ በቀጥታ የዜጎች ተሳትፎ በሚደረግ ምርጫ የተመረጡ የህዝብ ተወካዮች በሚገኙባቸው በሁለቱ ምክር ቤቶች ነው። የሪፐብሊኩ መንግስት አባላትም ራሳቸው ክልሎቹ እንደሆኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 47 ተደንግጓል። የፌዴራል መንግስቱ የመጨረሻ የስልጣን አካላት ስለሆኑት ሁለቱ ምክር ቤቶች የምክር ቤት አባላት ውክልና መሰረትም የአገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፍትሃዊ ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ እንደሆነ ይገልፃል። በዚሁ መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት  በአንቀፅ 94 መሰረት አባላቱ ሁሉን አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛና ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርአት እንደሆነ ይደነግጋል። ያም ሆኖ ግን የአብላጫ ድምጽ የምርጫ ስርአቱ በተለያዩ እና በሚበዙ የፓርቲዎች ችግር በየምክር ቤቱ ሁሉንም ድምጽ ሊወክሉ በሚችሉ ወንበሮች ሊያዝ አልተቻለም። በዚህም በርካታ ሮሮዎችና ቅሬታዎች መደመጣቸውን ታሳቢ በማድረግ ከላይ የተመለከተውን መንግስታዊ ተልእኮ ማሳካት የሚያስችል ስርአት ለማበጀት ታስቦ ገዢውና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርድር ጀምረዋል። ያም ሆኖ ግን በድርድሩ አስፈላጊነትና ሊያስገኝ በሚገባው ውጤት ላይ በድርድሩ ቅድመ ውይይት ላይ ተካፋይ የነበሩ ፓርቲዎች ብዙ ልዩነቶች እያንጸባረቁ  እና ይልቁንም ለፓርቲዎች ደረጃ እያወጡ ከእኛ ጋር እንጂ ከነዚህ ጋር ድርድር አያሻም የሚሉ ጽንፈኛና የህዝብን ተጠቃሚነት የሚቃረን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያስቀምጡ ፓርቲዎች ታይተዋል።

በአንድ ትውልድ የተጣመመ የፖለቲካ ግንኙነት ነው እዚህ አገር ውስጥ ያለው፡፡ ይህ የተጣመመ የፖለቲካ ግንኙነት እየቀጠለ ነው ያለው፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት በአገራችን የፖለቲካ ፓርቲ መሥርተው የሚታገሉት አብዛኞቹ የግራ ፖለቲካ አራማጅ የነበሩ ናቸው፡፡ የዚያን ጊዜ የነበረ ቁርሾ መቀጠል አለበት? እንዴት ነው አዲሱ ትውልድ የዚህ ቁርሾ ተሸካሚ እንዳይሆን ማድረግ የምንችለው? በራሱ የሚያስብና ራሱ ባመነጨው አዲስ አስተሳሰብ ውስጥ የሚኖር ትውልድ እንዴት ነው መፍጠር የምንችለው?

የሚለው እና ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በመጋቢት ወር 2008 ዓ.ም. ከዩኒቨርሲቲ ምሁራንና ከሌሎች ተመራማሪዎች ጋር አገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በተወያዩበት ወቅት ለውይይቱ መጀመሪያ ያደረጉት ጥያቄ አዘል ንግግር መልስ እንዳላገኘና አሁንም የተጣመመውን የፖለቲካ ግንኙነት ለማስቀጠል በሚተጉ ሃይሎች የተቃውሞው ፖለቲካ እንደተወረረ የሚያረጋግጥ ነው።

በገዢው ፓርቲ ሃገራዊ አቋምና ጥሪ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ጋር የጀመሩት ድርድርና ውይይት ፋይዳው ምንድን ነው? የሚለውን ከመመልከት አስቀድሞ ውጤቱን አሉታዊ እንደሆነ በማስወራት ከወዲሁ እንቅፋት ለመሆን እየተሸረበ ያለው ሴራም የዚሁ የጠማማ ፖለቲካ እና ፖለቲከኝነት መገለጫ ነው። አሁን ሀገሪቱ የምትተዳደረው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንጂ በመደበኛ ህግ አይደለም፡፡ ይሄ የሆነበት ምክንያት የአገሪቱ ሕዝቦች በሰላማዊ መንገድ ያቀረቡት ቅሬታን በመጥለፍ ወደ ሁከትና አውዳሚ እንቅስቃሴ ለመቀየር የተረባረቡ የውጭ ኃይሎች በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ውድመት በማስከተላቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያ በህዳሴ ጉዞ ላይ መሆኗን የማይቀበሉ ሃገሮች ሊያተራምሱን በስፋት መንቀሳቀሳቸውና አሁንም እየተንቀሳቀሱ መሆኑ፤ ይህንንም በመደበኛው ህግ ለመቆጣጠር ያልተቻለ መሆኑ ሌላኛው እና ተያያዥ የሆነው ምክንያት ነው።

ከነዚህ ሃይሎች ባሻገርም ከጽንፈኛ ዳያስፖራዎች ጀምሮ በአባይ ወንዛችን ላይ የተጠቃሚነት መብታችንን ለማረጋገጥ የጀመርነውን እንቅስቃሴ ለማኮላሸት የሚንቀሳቀሱ ሃይሎችን ሴራ ለማክሸፍም ሁነኛ መፍትሄ ሆኖ በመገኘቱም ነው።

ወጣቶችን የጥፋት ሐሳብ፣ ክብሪትና ነዳጅ እያስታጠቁ ለአገሪቱ ቁልፍ የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ያላቸውን ፋብሪካዎች፣ የአበባ እርሻዎችና ሌሎች ተቋማት በማጋየት ከፍተኛ ውድመት ማስከተላቸውም በተመሳሳይ፡፡ የአነግና የግንቦት ሰባት መሪዎች ከግብፅ መንግሥት ተቋማት ጋር እጅና ጓንት በመሆን ባቀነባበሩት የጥፋት እንቅስቃሴ በርካታ አገራዊና የውጭ ባለሀብቶችና ሠራተኞቻቸውን ለአደጋ ያጋለጠ የታሰበበት ከፍተኛ ውድመት መፈጸማቸውም በተመሳሳይ፡፡ እኒህና መሰል የጥፋት ዘመቻዎች በተጠናከረ እና በተጠና አግባብ በተፈጸሙበት አግባብ በነባሩ የህግ አግባብ ጉዳዩን መቆጣጠር የማይቻል መሆኑ በጥቅሉ ለአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መታወጅ አበይት ምክንያቶች ናቸው ።

እነዚህን የተጠለፉ ቅሬታዎች  ተከትሎ መንግስት በየደረጃው ካደረጋቸው ህዝባዊ ውይይቶች በመነሳት መሻሻል ያለባቸውን ለማሻሻልና የሚወገዱትን ህግና አሰራሮች ለማስወገድ ቁርጠኛ አቋም ከያዘባቸው ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በሚደረግ ድርድር የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርአቱ የሚጎለብትበትን እና ብሄራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል ስርአት መዘርጋት ነው። ያም ሆኖ ግን በድርድር ቅድመ ውይይቱ ግና አዋጁን ከማውገዝ ጀምሮ በቅድመ ሁኔታነት ያስቀመጡ እና በአዋጁ አግባብ የታሰሩ የህግ ታራሚዎችን እንደፖለቲካ እስረኞች ወስደው ይፈቱልን በሚሉ ቅድመ ሁኔታዎች ፖለቲካውን ለማጣመም የሚተጉ ተደራዳሪዎች በመድረኮቹ ላይ ታይተዋል።

በስልጡን ፖለቲካ እና ማህበረሰብ ውስጥ ምንም አይነት ችግሮችም ሆኑ ፖለቲካዊ ቅሬታዎች ሲኖሩ የሚፈቱት የህብረተሰቡን ጥቅምና ፍላጎት ከሚወክሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በመደራደርና በመወያየት ነው፡፡ የተሻለው የመፍትሄ መንገድም ይሄ ነው፡፡ ስለዚህ ገዢው ፓርቲ ያቀረበው የድርድር ጥሪ አስፈላጊነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፓርቲዎች አንድ ላይ ቁጭ ብለው መወያየት፣ መከራከርና ተደራድሮ አንድ ውጤት ላይ መድረስ ያለባቸው ጊዜ ላይ መሆናችንን የሚያሳይ ነው።

እያንዳንዱ ፓርቲ ይስፋም ይጥበብም የየራሱ ማህበራዊ መሰረት አለው፡፡ ህዝባዊ የድጋፍ መጠኑም ከፓርቲ ፓርቲ ሊለያይ ይችል እንደሁ እንጂ የሚወክሉት ድምጽ አላቸው፡፡ የቀረበው ጥሪም ይህን የሚያረጋግጥ ስርአት ለመዘርጋት ነው። በሌላ በኩልም  ያለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ይህቺ ሀገር የትም ልትደርስ አትችልምና ነው፡፡ በፓርቲዎች ያልተወከለ የፖለቲካ አስተሳሰብ የትም ሊደርስ አይችልም፡፡ ህብረተሰቡ ይሄን አውቆ የእሱን አስተሳሰብና አመለካከት ሊወክል የሚችል ጠንካራ ፓርቲ እንዲፈጠር የመጠየቅ ችግር ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቃዋሚዎቹ በድርድር መድረኩ ላይ እንኳ በአንድነት ለመሰለፍ አለመፈለጋቸውና እርስ በእርስ ከመናቆር አለመውጣታቸው የሚያሸማቅቅና ጠማማውም በቃህ ሊባል የሚገባው ሰአት ላይ መገኘታችንን የሚያመላክት ነው ።

ድርድሩ ያስፈለገው ችግሮች ስላሉና መፈታት ስላለባቸው ነው፡፡ ቢሆን እንኳ የ“ፖለቲከኞች መታሰር”ና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የሚያሳየው፣ የድርድር አስፈላጊነትን  እንጂ ለድርድር እንቅፋትነትን ወይም ቅድመ ሁኔታዎችን አይደለም፡፡ ይሄ ከሆነ እነዚህንና ሌሎች የሀገሪቱ ችግሮችን የድርድሩ አጀንዳ አድርጎ ውጤት ማምጣት እንጂ ከወዲሁ መጣመም ህዝባዊነትን አያመለክትም፡፡ ይህ ድርድር የሚካሄደው ለማንም አይደለም፤ ለህዝቡና ለሃገሪቱ ነው፡፡ ችግሮችንና ቅራኔዎችን ለመፍታት ነው። በመሆኑም፣ የውይቱም ሆነ የድርድሩ ልዩ ትኩረት የህዝዝቡ ፍላጎት ላይ ማተኮር አለበት። ይህ ከሆነ  ደግሞ ድርድሩን ህዝቡ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሊከታተለውና የተጣመመውን ሊያቃና አልያም በቃህ ሊለው መዘጋጀት አለበት ፡፡